legal aiddc

መ ብ ት ዎ ን ይ ወ ቁ

# ለተቸገሩ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ድጎማ (ታንፍ)

## TANF [ታንፍ] ምን ማለት ነው?

ታንፍ ከልጆች ጋር ለሚኖሩ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች የሚሰጥ ድጎማ ነው።

## TANF [ታንፍ] ማግኘት ይችላሉ?

የሚከተሉት ነገሮች ከተሟሉ በዲሲ ውስጥ TANF [ታንፍ] ማግኘት ይችላሉ፦

- በዲሲ ውስጥ ነዋሪ ከሆኑ።
- እርጉዝ ከሆኑ ወይም ዕድሚያቸው 18 ወይምዚያ በታች የሆኑ ልጆች ያልዎት ከሆነ
- ከመጨረሻው ወርሃዊ የገቢ መጠን በታች የሚያገኙ ከሆነ (ከታች ይመልከቱ)
- በጥሬ ገንዘብ ወይም የባንክ አካውንትዎ ውስጥ ከ$3,000 ያነሰ ገንዘብ ካልዎት (ዕድሚያቸው ከ60 ዓመት በላይ የሚሆኑ በቤተሰብዎ ውስጥ ለሚኖሩ አንድ ሰው ደግሞ ከ$4500 በታች ያነሰ)
- የአሜሪካ ዜግነት ያልዎት ከሆነ ወይም የተለየ ምድብ ላይ የሚመደቡ ከሆነ (ከታች ይመልከቱ)

| የቤተሰብ አባላት | የመጨረሻው ወርሃዊ ገቢ* | የመጨረሻው ወርሃዊ ጥቅማጥቅም |
|---|---|---|
| 1 | $664 | $504 |
| 2 | $789 | $629 |
| 3 | $963 | $803 |
| 4 | $1,143 | $983 |
| 5 | $1,296 | $1,136 |
| 6 | $1,495 | $1,335 |

*ታንፍ [TANF] ያልዎት ከሆነ ተጨማሪ ገንዘብ ማግኘት የጀመሩ ከሆነ፣ የእርስዎ TANF ድጎማ ማግኘት መቀጠል ይችላል። የልጆች ማቆያ ክፍያ [childcare] ወጪዎች ያልዎት ከሆነ መጠኑ ሊጨምር ይችላል።*

## TANF [ታንፍ] ያገኘሁኝ ከሆነ ምን ማድረግ ያስፈልገኛል?

TANF [ታንፍ] ያገኙ ከሆነ ሁለት ነገሮችን ማድረግ ይጠበቅቦታል፦

1. TANF [ታንፍ] በሚያገኙበት ወቅት የሥራ መፈለግ እንቅስቃሴ ማሳየት አለብዎ።
   - የሥራ መፈለግ እንቅስቃሳዎች ማለት፦ ሥራ፣ ትምህርት፣ ስልጠና፣ የስራ ፍለጋ። የስራ መፈለግ እንቅስቃሴዎች የማያሳዩ ከሆነ ጥቅማ ጥቅሞችዎ ሊቋረጡ ይችላሉ።
   - የሚከተሉትን የሚያሟሉ ከሆነ ሥራ መፈለግ እንቅስቃሴ ማሳየት አይጠበቅቦትም፦
     - የአካል ጉዳት ያለብዎ ከሆነ
     - ዕድሜው/ዋ ከ 1 ዓመት በታች የሆነ/ች ልጅ ያልዎት ከሆነ
     - የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባ ከሆኑ
     - በቤትዎ ውስጥ ለሚኖሩ የቤተሰብ ዓባላት እንክብካቤ እየሰጡ ከሆነ
     - የልጆች ማቆያ (child care) ሽፋን የሌልዎት ከሆነ
2. ወላጅ የሆኑ ከሆነ፣ የዲሲ መንግስት ከሌላኛው ወላጅ ላይ የልጅ ማሳዳጊያ የቀለብ ተቆራጭ መቀበል እንዲችል ማገዝ አለብዎ። እርስዎ ወይም ልጅዎ ይህንን በማድረግዎ ምክንያት ጉዳት የሚደርስባቹህ ከሆነ ይህንን ማድረግ አይጠበቆትም።

## እንግሊዘኛ ቋንቋ በሚገባ መናገር የማልችል ብሆንም ማመልከት እችላለሁ?

አዎ። ህጉ የሚለው በእርስዎ ቋንቋ መንግስት ሊያስተናግድዎት እንደሚገባ ነው። ምን ዓይነት ቋንቋ መጠቀም እንደሚችሉ ለኤጀንሲው ያሳውቁ።

## የአሜሪካ ዜጋ ያልሆንኩኝ ከሆነ TANF ማግኘት እችላለሁ?

**ምናልባት።** የአሜሪካ ዜጋ ያልሆኑ አንዳንድ ሰዎች TANF ማግኘት ይችላሉ።

TANF ማግኘት የማይችሉ ቢሆንም እንኳን፣ ለልጅዎ ወይም ለሌሎች የቤተሰብ አባላት ማመልከት ይችላሉ። የሚያመለክቱላቸውን ሰዎች የኢሚግሬሽን ሁኔታ መፃፍ ብቻ ይጠበቅቦታል። መንግስት ተጨማሪ ጥያቄዎችን ሊጠይቅ አይችልም።

# ፉድ ስታምፕስ ለማግኘት እንዴት ማመልከት እችላለሁኝ?

## ቅደም ተከተል 1፦ ሰነዶችዎን ያግኙ

ፉድ ስታምፕ፣ ታንፍ [TANF]፣ ሜዲኬድ [Medicaid]፣ እና የዲሲ ሐልዝኬር አሊያንስ [D.C. Healthcare Alliance] ጨምሮ **ለሁሉም** ጥቅማጥቅሞች **በተመሳሳይ ማመልከቻ** ላይ ማመልከት ይችላሉ። እነዚህን ሰነዶችን ማቅረብ አለብዎት። ኦርጅናሎቹን እንዳይልኩ! ሰነዶቹን ፎቶ ያንሱ ወይም ኮፒ ያድርጓቸው።

| ☑ | ☑ | ☑ | ☑ | ☑ |
|---|---|---|---|---|
| የመታወቂያ ፎቶ | የሶሻል ሴክዩሪቲ ካርድ (ያለዎት ከሆነ) | የገቢ ደረጃ ማረጋገጫ (ልክ እንደ ክፍያ መቀበያ ደረሰኞች) | የውሃ መብራት ጋዝ ፍጆታ ክፍያ ደረሰኝ ወይም ሌሎች የአድራሻ ማረጋገጫ | በእርስዎ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው የልደት ምስክር ወረቀት |

## ቅደም ተከተል 2፦ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን መንገድ በመምረጥ ማመልከቻዎን ይሙሉ፦

1. **በአካል በመቅረብ፦** ከእነዚህ ESA አገልግሎት ማዕከሎች ውስጥ አንዱ ላይ በመሄድ። በሚያመለክቱበት ሰዓት ደረሰኝ ይጠይቁ።

| **Anacostia Service Center** | **Congress Heights Service Center** | **H Street Service Center** | **Fort Davis Service Center** | **Taylor Street Service Center** |
|---|---|---|---|---|
| 2100 Martin Luther King Jr. Ave. SE | 4001 South Capitol St. SW | 645 H St. NE | 3851 Alabama Ave. SE | 1207 Taylor St. NW |
| (202) 645-4614 | (202) 645-4546 | (202) 698-4350 | (202) 645-4500 | (202) 576-8000 |

2. **በስማርት ስልክ፦** የDistrict Direct [ዲስትሪክት ዳይሬክት] መተግበሪያን ከመተግበሪያ መደብር ላይ ያውርዱ። በስልክዎ በኩል ያመልክቱ። የእርስዎን የማረጋገጫ ቁጥር ይፃፉ።
3. **ኦንላይን [በመስመር ላይ]፦** በDistrict Direct በኩል በድር ጣቢያ አድራሻ districtdirect.dc.gov/ua ላይ በመሄድ ኦንላይን [በመስመር ላይ] ያመልክቱ የእርስዎን ማረጋገጫ ቁጥር ጽፈው ያስቀምጡ። ያስገቡትን ማመልከቻ ቅጂ ያስቀምጡ።
4. **ደብዳቤ፦** dhs.dc.gov/page/apply-recertify-benefits ላይ ያለውን ማመልከቻ ያትሙ። ማመልከቻውን እና የሰነዶችዎን ቅጂዎች ለአገልግሎት ማዕከል (ከታች ለተጠቀሱት) ይላኩ። ማመልከቻዎን በደብዳቤ እንደላኩ የሚያሳየውን ማረጋገጫ ያስቀምጡ። (ይህ አማራጭ አይመከርም።)
5. **ፋክስ፦** dhs.dc.gov/page/apply-recertify-benefits ላይ ያለውን ማመልከቻ ያትሙ። የተሞላውን ማመልከቻ ወደ DHS ESA በፋክስ ቁጥር (202) 671-4400 ላይ ይላኩ።

# ካመለከትኩኝ በኋላ፣ የእኔ ማመልከቻ ላይ ውሳኔ በምን ያህል ፍጥነት ማግኘት እችላለሁ?

በአብዛኛው፣ መንግስት የእርስዎን ማመልከቻ ላይ ምላሽ ለመስጠት 45 ቀናት ሊፈጅበት ይችላል። ብዙ ጊዜ የሚወስድ ከሆነ፣ ከላይ የተጠቀሱትን የESA አገልግሎት ማዕከሎችን ያነጋግሩ እና Legal Aid DC ያግኙ። የእርስዎ ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ ወይም ውድቅ ከተደረገ በደብዳቤ ወይም በመተግበሪያው ላይ ማስታወቂያ ይደርስዎታል።

# TANF [ታንፍ] አላገኙሁም ወይም TANF ድጎማ ቆሞብኛል። ምን ለማድረግ እችላለሁኝ?

ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለዎት። የእርስዎ ጥቅማጥቅሞች እንደተከለከለ፣ እንደተቀነሰ ወይም እንደተቋረጠ የሚገለጸው ማስታወቂያ በደረስዎ በ90 ቀናት ጊዜ ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ አለብዎ። ይግባኝ ለመጠየቅ ሶስት ቅድመ ተከተሎችን መጠቀም አለብዎ።

1. የይግባኝ መጠየቂያ ቅጹን በመስመር ላይ oah.dc.gov/node/154252 ያግኙ።
2. የይግባኝ መጠየቂያ ቅጹን ይሙሉ።
3. ከሚከተሉት መንገዶች ውስጥ <u>አንዱን</u> በመጠቀም ቅጹን ይሙሉ (ማመልከቻዎን በሚያስገቡበት ሰዓት ለራስዎ የቅጹን ቅጂ ሁልጊዜ ይሙሉ)፦
   - በዚህ ኢሜይል ይላኩ oah.filing@dc.gov
   - ለOffice of Administrative Hearings ቢሮ በአድራሻ 441 Fourth St. NW, Suite 450N ላይ ይዘው ቢሮ በአካል ይምጡ።
   - ከላይ የተጠቀሰው አድራሻ ላይ ለOffice of Administrative Hearings በደብዳቤ ይላኩት (ይህ አማራጭ አይመከርም)

የእርስዎ አቤቱታ እስከሚሰማ ድረስ የእርስዎን ጥቅማጥቅሞች ማግኘትዎን ሊቀጥሉ ይችላሉ። የእርስዎ ጥቅማ ጥቅሞች ከመቆረጣቸው ወይም ከመቀነሳቸው በፊት ጉዳዩ በአስተዳደር እንዲታይልዎት ይጠይቁ። አስቸኳይ ጉዳይ እንደሆነ ይግለጹ።